# «የጭን ቁስል »ልቦለድ ከእንስታዊነት ጽንስ ሃሳብ አንጻር


በ

ረድኤት አዳነ

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የማኅበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል


ነሃሴ 2013 ዓ.ም

# «የጭን ቁስል »ልቦለድ ከእንስታዊነት ጥንስ ሃሳብ አንጻር

በ

ረዳኤት አዳነ

የጥናቱ አማካሪ

ዳናይት ብርሃኑ

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

ነሃሴ **፩2013** ዓ.ም

# ምስጋና

በቅድሚያ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለልዑል እግዚሐብሔር እና ለእናቱ ለድንግል ማርያም ክብር እና ምስጋና ይሁን። እንዲሁም ምንም ሳትሰለች ፣እዉቀት ፣ምክርና ጊዜዋን ሳትሰስት ለሰጠችኝ ለመምህርት ዳናይት ብርሀኑ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነዉ።በመጨረሻም መረጃን ለሰጡኝ ፣ መፅሃፍ እንዲሁም ሀሳብ ለለገሱኝ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# አበርክቶ

በሀገራችን ኢትዮጵያ በጾታ ምክንያት ጥቃት ለደረሰባቸዉ ሴቶች በሙሉ እና ለባለ ታሪኳ ሰናይት ብርሀኑ መታሰቢያ ይሁንልኝ።

## አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ የጭን ቁስል ልቦለድ ከእንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር በሚል ርዕስ የቀረበ ነዉ። ጥናቱ የተሰራበት ዘዴም ገለፃዊ ሲሆን የተጠቀመችዉ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ መፅሐፉን በማንበብ እና ከጥናቷ ጋር ተያያዠነት ያላቸዉን ፅሑፎች በማንበብ ነዉ። ጥናቱ የሚያተኩረዉ ከእንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ሲሆን በዚህ ጥናት ላይም የተለያዩ ርዕሶችን በማንሳት የሴቶችን ጥቃት እና ጭቆና ለማህበረሰቡ በማዉጣት እንዲማርበት እና እንዲገነዘብበት ማስቻል እና ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ እንዲሁም ስነ አምሮአዊ ጫና ሚያደርሱትን ለማሳዬት ነዉ ዋና አላማዉ።

## የአማካሪዉ ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመርያ ድግሪ ማሞያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገላት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪዉ ስም……………

ፊርማ……………

ይህ በተማሪ ረድኤት አዳነ የጭን ቁስል ልቦለድ ከእንስታዊነት ፅንሰ ሃሳብ አንፃር በሚል ርዕስ

የተሰራዉን የመጀመርያ ድግሪ ማሞያ ፁሁፍ የዩኒቨርስቲዉን ጥራት ደረጃ ያሚላ እና ለቴአትር

ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነዉ፡፡ ይህም በፈታኝ ኮሚቴዉ

ተረጋግጧል፡፡

ፈታኝ አንድ ፊርሜ___________

ፈታኝ ሁለት ፊርሜ__________

ቀን___________

## ማዉጫ


ምዕራፍ አንድ........................................................................................................................... 1

1. መግቢያ ................................................................................................................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ....................................................................................................................... 1

1.2. የጥናቱ አላማ ..................................................................................................................... 1

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ.................................................................................................................. 2

1.4. የጥናቱ መጠነ ር ዕ ይ.......................................................................................................... 2

1.5. የጥናቱ ዘዴ ........................................................................ 2

1.6. ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች ........................................................................ 2

1.7. የጥናቱ አደረጃጀት........................................................................ 3

1.8.በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች........................................................................ 3

ም ዕራፍ ሁለት ........................................................................ 4

2. የፅንሰ ሀሣብ ቅኝት........................................................................ 4

2. 1.የልቦለድ ምንነት........................................................................ 4

2.2.የልቦለድ አላባዉያን ........................................................................ 4

2.3. የእንስታዊነት ምንነት........................................................................ 8

2.4. የእንስታዊነት ንቅናቄ አጀማመር........................................................................ 9

2.5.የእንስታዊነት አይነቶች ........................................................................ 10

2.6. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ........................................................................ 12

ምዕራፍ ሶስት........................................................................ 13

3.የመረጃ ትንተና........................................................................ 13

3.1.የጭን ቁስል ልቦለድ ታሪክ ........................................................................ 13

3.2. የጭን ቁስል ልቦለድ ላይ ሴቶች በምን መልኩ ተስለዋል........................................................................ 15

3.3.የጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ሴቶች ከእንስታዊነት አንፃር እንዴት ተገልፀዋል፧ ........................................................................ 15

3. 4. የጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ሴቶች የሚደርስባቸዉ ጫና ምን ይመስላል፧........................................................................ 17

3.5. የጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ -ባህርያት........................................................................ 21

ከሊብራል እንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንፃር፧ ........................................................................ 21

ምዕራፍ አራት........................................................................ 22

4. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ........................................................................ 22

4.1.ማጠቃለያ ........................................................................ 22

4.2.የመፍትሔ ሀሳብ ........................................................................ 23

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸዉ ........................................................................ 24

ዋቢ መፅሐፍት ....................................................................................................................................... 26

## ምዕራፍ አንድ

# 1. መግቢያ

ስነጽሁፍ ማነኛዉንም በሰዉ ልጅ ገጠመኝ የተከሰተንና ሊከሰት የሚችልን ነገር እንዲሁም በሰዉ የምናብ አድማስ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብን ነገር ሁሉ ሊያካትት ይችላል። መጠነርእዩእጅግ ሰፊ ብቻ ሳይሆን ገደብ አልባም ነዉ። የሰዉ ልጅ አያሌ ተግባራትን ፣ በምዕናቡ የሚፈጥረዉ አለምና የአለሙ ፍጡራን ፣ በሰዉና በሰዉ መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ፣ በሰዉና በማህበረሰብ ፣ በሰዉና በእንስሳት ፣ በሰዉና በተፈጥሮ መካከል የሚፈጠሩ ግንኙነቶችን በስነጹሁፍ ዉስጥ እንደአስፈላጊነታቸዉ ሊካተቱ ይችላሉ። በአጠቃላይ ስነጹሁፍ የሚቀዳዉ ከሰዉና ከተፈጥሮ በመሆኑ ምንጩ የማይደርቅና ዘላለማዊ ነዉ። ይህም በመሆኑ በስነጹሁፍ ላይባል የሚችል ነገር የለም ማለት ነዉ። በስነጹሁፍ ላይባል የሚችል ነገር የለም ሲባል ግን ሁሉም ነገር ተግበስብሶ እንዳለ በጥሬዉ ይቀመጣል ማለት አይደለም። ( ዘሪሁን አስፋዉ ፣ 2005 ፣ 3 )

ልቦለድ ሰፍ ያለ መጠነ ርዕይ ያለዉ በመሆኑ ለደራሲዉ ያልተገደበ ነፃነት ይሰጠዋል። ልቦለድ ማህበራዊ ሒወትን በስፋት በሚጥምና በሚስብ መልኩ የማሳየት አቅም ያለዉ የሰዉን ልጅ አያሌ ገጠመኞችን ማሳየት የሚችል ኪነጥበባዊ ቅርፅ ነዉ ።

## 1. 1. የጥናቱ ዳራ

አጥኝዋ የጭን ቁስል ልቦለድ ላይ ልትሰራ ያነሳሳት ምክንያት ልቦለዱ የሴቶችን ጭቆናና በደል ስለሚያሳይ ነዉ። ሆኖም በጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ ባህሪያት የሚያሳልፉት የእለት እለት የኑሮ ሁኔታ በጣም የሚያስከፋ በመሆኑ ዋናዋ ገፀባህሪ ጥንካሬዋን በመመልከት ይህንን ልቦለድ ከእንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ቢሰራ የብዙ ሴቶችን ሒወት ያሳያል ብላ በማሰቧ ነዉ።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

## 1.2.1.የጥናቱ አብይ አላማ

- ❖ በጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ - ባህርያትን ከእንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ ትንተና ማድረግ።
- ❖ የጭን ቁስል የተሰኘዉ ልቦለድ ከእንስታዊነት አንፃር ትንተና ማድረግ።

### 1.2.2.የጥናቱ ንዑስ አላማ

- ❖ በጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ-ባህርያት የደረሰዉን ጫና ማሳወቅ ፡፡
- ❖ ስለ ጭን ቁስል ልቦለድ ትንተና መስጠት፡፡

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

የጥናቱ መካሔድ በረካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡ ከነዚህም ዉስጥ ጥናታዊ ፁሁፉን አግኝተዉ ለሚያነቡ አንባቢዎች ስለ እንስታዊነት ምንነት ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም በአገራችን ያሉ ሴቶች ምን ያህል ጫና በወንዶች እንደሚደርስባቸዉ ጭምር ለማሳወቅ ይረዳል፡፡

## 1.4. የጥናቱ መጠነ ር ዕ ይ

ይህ ጥናት በደራሲ ተከሉ ጥላሁን የተፃፈዉ እና በ 2012 ዓ.ም ለ 28ኛ ጊዜ የታተመዉ የጭን ቁስል መፅሐፍት ዉስጥ ያሉ የሴት ገፀ ባህርያትን ከእንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንፃር ይተነትናል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዘዴ

አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ልቦለዱን ደጋግማ በማንበብና እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ መሠብሰቢያ ዘዴ በመጠቀም ማለትም መፅሀፍትን በማንቡብ እና ከዚህ ቀደም የተሰሩ ጥናታዊ ፅሁፎችን በመፈተሸ ትተነትናለች፡፡ አጥኝዋ የምታጠናዉ ጥናታዊ ፅሁፍ ገላጭ ከሚባለዉ ጥናቲዊ ፅሁፍ ይመደባል፡፡ ያለዉ እንዳወቅ ሙሉ (ፕሮፌሰረ) « የምርምር መሰረታዊ መርሆች »በሚለዉ መፅሀፉ ዉስጥ ስለ ገላጭ ምርምር እንዲህ ይላል፡፡ ገላጭ ምርምር ስሙ እንደሚያመለክተዉ

ተመራማሪዉ አንድ ጉዳይ አንስቶ ችግሩ ምን ያህል አሳሳቢ እንደሆነ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ መሠረት አድርጎ የሚያቀርብበት ነዉ፡፡ (2009 ፣21) ስለሆነም አጥኝዋ የጭን ቁስል ልቦለድ ከእንስታዊነት ጽንሰሃሳብ አንፃር ትተነትናለች ፡፡

## 1.6. ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄዎች

- ❖ የጭን ቁስል ልቦለድ ላይ ሴቶች በምን መልኩ ተስለዋል፧
- ❖ የጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ሴቶች ከእንስታዊነት አንፃር እንዴት ተገልፀዋል ፧

❖ የጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ሴቶች የሚደርስባቸዉ ጫና ምን ይመስላል ፟?

❖ የጭን ቁስል ልቦለድ ላይ ያሉ ሴት ገፀ- ባህርያት ከሊብራል እንስታዊነት ጽንሰ ሀሳብ አንፃር?

## 1.7. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአራት ምዕራፎች ተከፍሏል። በምዕራፍ አንድ ላይ መግቢያ ፣ የጥናቱዳራ ፣ የጥናቱ አላማ ፣ የጥናቱ አብይ አላማ ፣ የጥናቱ ንዑስ አላማ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸዉ ጥያቄወች ፣ የጥናቱ አወቃቀርን ይጨምራል ። ምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ስራወች ቅኝት እና የፅንሰ ሀሳብ ትንተናን ይይዛል። ምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና እና ምዕራፍ አራት የጥናቱ ማጠቃለያ ግኝት፣ የጥናቱ ማጠቃለያ መፍትሔ፣የመፍትሔ ሀሳቦች፣ ዋቢ መፅሀፍትን እናአባሪን ጨምሮ ያስቀምጣል።

## 1.8.በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኚዋ በዋናነት ይህን ጥናት ለመስራት የገጠማት ችግር የጊዜ መጣበብ እና ከጥናታዊ ፅሁፋ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉን በቂ መፅሐፍቶችን መመልከትና ማግኘት አልቻለችም ነበር።

## ም ዕራፍ ሁለት

## 2. የፅንሰ ሀሣብ ቅኝት

## 2. 1.የልቦለድ ምንነት

ልቦለድ ማለት የደራሲዉ የምናባዊ የፈጠራ ዉጤት ሲሆን አንድ በምናብ ያለ የሒወት እንቅስቃሴ ፈጠራን ቁልጭ አድርጎ እዉነታዉን የሚያሳይልን የኪነ ጥበብ ዘርፍ ሲሆን በሰዉ ልጅ ሒወት ዉስጥ በማህበራዊ ፣ በኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ጭምር የሚያሳይልን ነዉ ። የልቦለድ ደራሲ ልቦለድን ሲፅፍ በማህበረሰቡ ህይወት ዉስጥ የኖረን ወይም ይፈጠራል ብሎ በማመን ነዉ። በማህበረሰቡ ዉስጥ የሌሉ ምናባዊ (**ኘመአገኘነአረየ**) ፣ ሳይንሳዊ (**ሰሡኘጠነተኘፈኘሡ**) ወይም ኢ-ተፈጥሮአዊ **ሰሀፐጠረ ነአተሀረአለ** የፈጠራ አይነቶች ወይም የልቦለድ አፃፃፍ መንገዶች አሉ።

> ልቦለድ ማህበራዊ ህይወትን በስፋት በሚጥምና በሚስብ ዘይቤ የማሳየት አቅም ያለዉ የሰዉን ልጅ አያሌ ገጠመኞችን ማቅረብ የሚችል ኪነ -ጥበባዊ ቅርፅ ነዉ። ከሌሎች የስነ - ፅሁፍ ዘርፎች የበለጠ ዘላቂነት ያላቸዉ የተስፋፉና የበለፀጉ የሰዎች ምስሎችን የመያዝ አቅም አለዉ። በልቦለድ የሰዉ ልጅ ሀዘን ደስታ፣ጥላቻ ፍቅር ፣ ምኞት ፍላጎት ፣ ብልፅግናና ዉድቀት በአጠቃላይ ግብሩ እና አተያዩ በኪነታዊ ዘዴ ይቀርባል። የልቦለድ ደራሲ የሰዉን ልጅ የተለያዩ የሒወት ፈርጆች በኪነታዊ ቋንቋ በሚያቀርብበት ጊዜ የራሱን አመለካከት በመመርኮዝ ነዉ **ፅ**ልቦለድ ደራሲዉ ለህይወት የሚሰጠዉ የግል ትርጓሜ ነዉ። ( ዘሪሁን አስፋዉ ፣ **2005**፣ **154**)

## 2.2.የልቦለድ አላባዉያን

### <u>2.2.1.</u>ታሪክ

ታሪክ በድርጊት ቅደም ተከተል እየተተረከ የተደራሲያንን ስሜት የሚይዝ ነዉ። ታሪክ የልቦለድ ቀዳሚና ዋነኛ ነገር ነዉ። አንድን ልቦለድ ልቦለድ ከሚያስብሉት ነገሮች መሀል ቀዳሚዉና ዋነኛዉ ነገር ታሪክ ነዉ። ታሪክ በጊዜ ቅደም ተከተል የሚቀርብ የልቦለድ አይነት ነዉ።

ታሪክ በሰዉ ልጅ ገጠመኝ ሊከሰት የሚችል ወይም የሰዉ ልጅ በምናቡ ሊያስበዉና ሊፈጥረዉ የሚችል ሲሆን የአንባቢን አዕምሮ ፈቅዶ ይቀበለዋል። በእዉኑ አለም በሰወች

ዘንድ ሊያጋጥም የሚችልን ድርጊት ወይም የህይወት አቅጣጫ ወይም የኑሮ መልክ ሲያመጣ ታአማኒ ይሆናል። ታሪክ ደራሲዉ በመረጠዉ የጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ተቀናጅተዉ የሚያቀርቡትንና በገፀ- ባህርያቱ የሚፈፅሙትን ድርጊቶች አነሳስ ፣አፈፃፀምና የመጨረሻ ዉጤት ይይዛል። እነዚህ ሁሉ ከሰዉ ልጅ ልዩ ልዩ ገጠመኞች የተቀዱ መሆን ይኖርባቸዋል። ቅጅዉ በእዉነት ላይ የተመሠረተ ከሆነ የታሪኩ ታአማኒነት ከፍ ያለ ይሆናል። የልቦለድ ታሪክ ታአማኒነቱ ብቻ ሳይሆን አጓጊነት ሊኖረዉ ይገባል። ( ዘሪሁን አስፋዉ፣ **2005 ፣ 156**)

## 2.2.2.ግጭት

ግጭት በአንድ ልቦለድ ታሪክ ዉስጥ መጀመርያ ፣ መሀል ወይም መጨረሻ ላይ የሚፈጠር የገፀባህርያት ፍላጎቶቻቸዉ ሳይመጣጣን እና ሳይሳካ ሲቀር ቅራኔ መፍጠር ማለትም ትአማኒነት ፣አንድነት ፣ ሚዛናዊነት እና ጠቀሜታዎች አለመኖር ነዉ። ለምሳሌ፦ ሰዉ ከሰዉ ጋር ሰዉ ከተፈጥሮ ጋር ሰዉ ከማህበረሰቡ ጋር እንዲሁም ሰዉ ከፈጣሪዉ ጋር የሚገጩ ይሆናል።

> ግጭት በእዉኑ አለም በሰወች ሒወት ወይም ገጠመኝ የተለያዩ ዉጣ ዉረዶችን እና ትግሎች ያጋጥማሉ እነዚህ ዉጣ ዉረዶች እና ትግሎች በሒወት ለመኖር ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት የተሻለዉን ለመያዝ የተመኙትን ለማሳካት በአጠቃላይ ፍላጎትን ለማሟላት ወይም የልብን ለማድረስ የሚደረጉ ናቸዉ ለማለት ይቻላል። ለመኖርም ሆነ የዉስጥ ፍላጎትን ለማሟላት ሲባል በሰወች ዘንድ በሚፈጠሩ ልዩ ልዩ ግንኙነቶች ምክንያት ቅራኔወች ወይም አለመጣጣሞች በሁለት ወገኖች መካከል ሲፈጠሩ ይታያል። ( ዘሪሁን አሰፍዉ፣ **2005፣ 172**)

## 2.2.3.መቼት

መቼት ጊዜና ቦታን የሚገልፅልን በተጨማሪም በታሪኩ መግቢያ በየምዕራፎቹ ወይም በየክፍሎቹ መጀመርያ እና በድርጊት መሀል መሀል ላይ ከታሪኩ ጋር ተሰባጥሮ የምናገኘዉ እንዲሁም ከጊዜና ከቦታ ባሻገር ማህበራዊ እዉነታን የሚያሳይልን ነዉ ። «ፈ መቼት ታሪኩ የተከናወነበትን ገፀ - ባህርያቱ የሚኖሩበት ወይም የገጠር ወይም የከተማ አካባቢ ብቻ አይደለም አያሌ ነገሮችን ይጨምራል ከገጠሩና ከከተማዉ ሒወታዊ እንቅስቃሴ ጋር ያሉትን የተለያዩ ሁኔታወች አካቶ በመያዙም ጓዘ ብዙ ነዉ። »( ዘሪሁን አስፋዉ ፣**2005 ፣ 179**)

« መቼትን መቼት ከሚያሰኙት የድርጊቱ ጊዜ የድርጊቱ ቦታ እና ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ ያለዉ ማህበራዊ እዉነታ ናቸዉ። መቼትን **ዐ**መቼ **ዐ** እና **ዐ**የት **ዐ** የሚሉ ድርጊቱ ቦታና ጊዜ ብቻ የሚያመለክቱትን ሁለት ቃላት አዳብሎ በመተርጎም ሶስተኛዉን ነጥብ አይጨምረዉም። መቼት አጠቃላይ እና ወስን በሚሉ ሁለት ክፍሎች ይከፈላል። »(ፋንታሁን እንግዳ ፣1993፣ 25)

## 2.2.4.ጭብጥ

ጭብጥ ደራሲዉ ለተደራሲያን ወይም ለተመልካች ሊያስተላልፈዉ የፈለገዉን ያስተምራል ፣ ያዝናናል ፣ ቁም ነገር ያስጨብጣል ብሎ ያሰበዉን ዋነኛ መልክት ጭብጥ ይባላል። ጭብጥ ለአንድ ልቦለድ አስፈላጊና ዋነኛ ነገር ነዉ።

> ጭብጥ በስነ ፅሁፍ ስራዎች ማለትም በተዉኔት ፣በልቦለድ እና በግጥም ፈጠራዎች ዉስጥ ማዕከላዊ ወይም ገዥ የሚባለዉ ረቂቅ ሀሳብ ነዉ ። በመደበኛ እና በኢ መደበኛ ወጎች እና እንዲሁም በሌሎች ታሪካዊ ሀይማኖታዊ ፣ ሥነ ፍጥረዊ ፣ፍልስፍናዊ እና ሳይንሳዊ ፅሁፎችን ዘንድ ጭብጥ የሚባለዉ የመወያያዉ አጠቃላይ ርዕስ ወይም ርዕሰ ጉዳይ ነዉ። በምዕናባዊም ሆነ በኢ - ምናባዊ ስነ ፅሁፍ አንዳንድ ጊዜ የማነኛዉም ፅሁፍ ጭብጥ በርዕሱ ላይ በግልፅ ተብራርቶ ይገኛል። ( ፋንታሁን እንግዳ ፣1993፣112)

«ጭብጥ በአጠቃላይየልቦለድ ታሪክ ተጨምቆ ወይም ተፈልቅቆ የሚወጣ የልቦለድ መልክት ነዉ። »( ብርሀኑ ገብረፃዲቅ ፣2008 ፣ 108)

## 2.2.5.ገፀ-ባህሪ

ገፀ- ባህሪ በፈጣራ ታሪክ ዉስጥ ያሉ ደራሲዉ የፈጠራቸዉ በገሀዱ አለም ያሉ ሰዎች ፣ እንስሳት ፣ሰማያዊ ወይም ተፈጥሮአዊ ፍጥረታት መናፍስት እንዲሁም ተንኮልን ፣ ክፋትን ፣ ምቀኝነትን ፣ ደግነትን እና ቁንጅናን እነዚህን ያጠቃልላል።

> ገፀ - ባህሪያት በልቦለድ አለም ስጋ ለብሰዉ ፣ ባህሪይ ተጎናፅፈዉ ፣ መጠርያ ተሰጥቷቸዉ ፣ መኖርያ ተበጅቶላቸዉ የሚንቀሳቀሱ ፣የሚተነፍሱ ፣የሚናገሩ ፣ የሚበሉ ፣የሚጠጡ እንደ እዉኑ አለም ሰወች የሚኖሩ ፣ የሚሞቱ ፣ የሚርባቸዉ ፣ የሚጠማቸዉ ፣ የሚፍቀሩ ፣ የሚጣሉ ፣ የሚደሰቱና የሚያዝኑ የልቦለድ አለም ሰወች ናቸዉ።

ገፀ - ባህሪያት ከቀረበበት ቦታና ዘመን የፈለቁ የዚያዉ ቦታና ዘመን ሰወች ወኪሎች ቢሆኑ በዘመኑ የነበረዉን አስተሳሰብና አጠቃላይ አተያይ ባህልና ማህበራዊ ልምድ መንፈሳዊ ቁሳሳዊ ሁኔታ ያንፀባርቃሉ። ( ዘሪሁን አስፋዉ ፣2005 ፤160)

ገፀ- ባህርያት ተዉኔቱን ለማራመድ በፅሐፊዉ የተፈጠሩ እና በድርሰቱ ዉስጥ የሚኖሩ የድርጊት ወኪሎች ናቸዉ። እያንዳንዱ ገፀ - ባህሪ ከሌላዉ ገፀ - ባህሪ በግልፅ የተለየ ማንነት ሊኖረዉ ይገባል። በእድሜ ፣ በአቋም ጰ በተክለ ሰዉነት ጰ፣ በእምነት ፣በአስተዳደግ ወይም በአነጋገር ጰቋንቋ ጰ ወዘተ ልንለያቸዉ ይገባል። (ጫንያለዉ ወጰጊወርጊስ እና ሌሎቹ ፣ 2009 ፣42)

## 2.2.6. ትልም ዅ ሴራ

በአንድ ልቦለድ ታሪክ ዉስጥ ከመጀመርያዉ እስከመጨረሻዉ ያለዉን ነገር ምክንያትና ዉጤትን ያሳየናል።

> በአንድ ልቦለድ ዉስጥ ምን ጵ ለምን ተደረገ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘዉ መልስ የሚያካትት ወይም በጊ ዜ ቅደም ተከተል የተፈፀሙ ሁነቶች የተደረጉበትን ምክንያት እና የሚያስከትሉትን ዉጤት ጥብቅ ቁርኝት የያዘ የልቦለድ አካል ሲሆን ያንድ ልቦለድ ትልም መሠረት አቀንቃኙ ወይም አቀንቃኟ ገፀ- ባህሪ የሚፈ ፈፅሚየዉ ድርጊቶች እና የደራሲዉ ዋነኛ አላማ ናቸዉ። ስለዚህም የገፀ- ባህሪያቱ ስብዕናና ስነ ልቦናዊ መልክ የሚገቧቸዉ ሁነቶች እና ከማህበራዊ አካባቢያቸዉ ጋር ባለዉ ግንኙነት ምክንያት የሚፈፅሟቸዉ ዋና ዋና ድርጊቶች እንዲሁም ልቦለድ ያቀፈዉ ማዕከላዊ አላማ በአንድ ተጣምረዉ ትልሙን ይመሠርቱታል ማለት ነዉ ። ( ዘሪሁን አስፋዉ ፣2005 ፣158-159)

«የሴራ ተግባር በአንፃሩ የድርጊቶች ቅደም ተከተል ሳያዛባ አንዱን አስቀድሞ አንዱን ሳያዘገይ በምክንያትና ዉጤት ላይ ተመስርቶ መተረክ ነዉ። » ( ፋንታሁን እንግዳ ፣ 2009 ፣ 41)

ሴራ ፡-በጭብጥ በተዉኔቱ ዉስጥ « ምንተባለጵ »የሚለዉን እንደምናገኘዉ ፤በሴራ ደግሞ «ምን ተፈጠረጵ » የሚለዉን እናዉቃለን። በሴራ ዉስጥ የሚፈጠሩ ድርጊቶች በራሳቸዉ ለራሳቸዉ የቆሙ ሳይሆኑ ፣እያንዳንዱ በግልፅ ከሌላዉ ጋር ህብረት ያላቸዉ መሆን አለባቸዉ። ( ጫንያለዉ ወጰጊወርጊስ እና ሌሎቹ ፣ 2009፣ 41)

## 2.2.7.አንፃር

አንፃር በደራሲዉና በተደራሲዉ መሀል ሆኖ ሁነቶችን ወይም ድርጊቶችን የሚገልፅልን እና የሚተረጉምልን ታርክ አንፃር እንለዋለን። በልቦለድ ዉስጥ ተራኪዉ ተሳታፊ ሁኖ ሲተርክ ወይም ከታሪኩ ዉጪ ሆኖ እንደታዛቢ ሊተርክ ይችላል።

> አንፃር ማነኛዉም ልቦለድ በደራሲና በአንባቢዉ መካከል ሆኖ ሁነቶችን የሚገልፅና የሚተረጉም አልፎ አልፎም በግልፅ አብዛኛዉን ጊዜ ግን በዉስጠታዋቂ የሚኖር የታሪኩን ሂደት እየተከታተለ የሚያቀርብ ተራኪ አለዉ። ተራኪ ታሪኩን የሚመለከተዉ ተሳታፊ ወይም ታሪኩ የማይመለከተዉ ታዛቢ ሊሆን ይችላል ። ተሳታፊ ከሆነ ታሪኩ የሱም ታሪክ በመሆኑ የራሱንም ሆነ ከሱ ጋር ግንኙነት ያላቸዉን ገፀ ባህርያት ታሪክ በሱዉ አመለካከት ያቀርባል። ታዛቢ ከሆነ ደግሞ ዳር ቆሞ ያዬዉን የታዘበዉን እንዳለ ነዉ የሚያቀርበዉ። አንዳንዱ ተራኪ የገፀ ባህርያትን ልዩ ልዩ ድርጊቶችና አጠቃላይ አኗኗር በሚገባ በማወቁ አንድም ሳይቀር ለአንባብያን ያቀርባል ። ( ዘሪሁን አስፋዉ ፣2005 ፣190)

«አንፃር በታሪኩ መሀል እየገባ ሁኖቶችን የሚገልፅ ነዉ። አንፃር ደራሲዉ ታሪኩን የሚያቀርብበት የትረካ አቅጣጫ ነዉ። እኔ እያለ ታሪኩን የሚያቀርብ እና የሚያሳዉቅ ከሆነ አንደኛ መደብ አንፃር ይባላል። »(ብርሀኑ ገብረፃዲቅ ፣ 2008 ፣ 108)

## 2.3. የእንስታዊነት ምንነት

እንስታዊነት ማለት ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ጫና እና በደል የሚቃረንና ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸዉ የሚል ንቅናቄ ነዉ። የእንስታዊነት ሴቶች በማነኛዉም ነገር ላይ ፡- በፖለቲካ ፣በማህበራዊ ፣ስነ-አዕምሮአዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጫና በወንዶች ሚደርሰዉን ለማስቆም የሚሰራ ሲሆን በነዚህ ተቋማት ላይ እኩል ተሳትፎ የማግኘት እንዳለባቸዉ እና ሴቶች ከወንዶች በማነኛዉም ስራ ላይ ተሰማርተዉ እኩል ሁነዉ መብታቸዉን ወንዶች እንዳይጋፏቸዉ ወይም እኩል መብት እንዳላቸዉ ማሳወቅ እና ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት እንዲኖራቸዉ ያደርጋል። እንስታዊነት ሴቶች በፈለጉት የሙያ ዘርፍ የመሳተፍ እና የፈለጉትን ነገር በራሳቸዉ ፍቃድ የማድርግ እና መብታቸዉን ጭምር እንዲያስከብሩ ያለመ ንቅናቄ ነዉ።

> እንስታዊነት ማለት ሰፍ ያለ ሀሳብ ሁኖ መነሻዉ የሆነዉ በዋነኝነት በጾታ እኩልነት ወይም በሴትና በወንድ እኩልነት ላይ ነዉ። እንስታዊነት በጾታ ምክንያት የሚደርሰዉን መገለል መነሻ አድርጎ የተመሠረተ እንቅስቃሴ ነዉ። በጾታ ምክንያት ያለዉ ክፍፍል ለብዙ አመታት አከራካሪ ሆኖ ቢቆይም የተወሰኑ ለዉጦች

ከበረካታ አመታት በኋላ መጥተዋል። የወንዶች አካላዊ ጥንካሬ እና ከልጅ አስተዳደር አኳያ ያላቸዉ ነፃነት ሴቶችን እንዲጨቁኑ እና ዝቅ አድርገዉ እንዲመለከቱ ምክንያት ነዉ። ይህ አይነት የወንዶች ተግባር ሴቶችን በሁሉ መስክ ተጠቂ ያደርጋቸዋል። እንስታዊነት ሴቶች በጾታ ምክንያት የሚያጡትን መብት ያስጠብቃል።በምዕራብ የተነሳዉ የእንስታዊነት ሀሳብ በበርካታ የአለም ሀገሮች በመሠራጨት የበረካታ ሴቶችን መብትና ጥቅም አስጠብቋል። በስሶስተኛዉ ከ ጳ ዘመን የሮም ሴቶች በሴቶች ላይ የተጣለዉን የዉድ እቃወችን ያለመጠቀም ህግ በመቃወም ያደረጉት እንቅስቃሴ አይነቱን እና መልኩን በማስፍት የእንስታዊነት እንቅስቃሴ ሆኖል። ( **ድረ ርእጅኝብእ ርእንኝእን ፥ 2019 ፥ 120)ቾ 1 ሽ**

ይህ የእንስታዊነት ንቅናቄ ፅንሰ ሀሳብ ሴቶች ከወንዶች እኩል እንደሆኑ እና ሴቶች እንደወንዶች በማህበረሰቡ ዘንድ እኩል እይታ እንዲፈጠርላቸዉ ማለትም በማህበራዊ ፥ በኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በፖለቲካዊ ዘንድ እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ ነዉ። በተጨማርም የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት እንዳላቸዉ እና በማነኛዉም ነገሮች ላይ እኩል የስራም ሆነ የትምህርት እድል ተሰጧቸዉ መሳተፍ እናም በተሳተፉት ነገሮች ላይ ዉጤታማ የመሆን እና መብታቸዉን ጭምር አስጠብቀዉ ከወንዶች እኩል ናቸዉ የሚል ነዉ ።

## 2.4. የእንስታዊነት ንቅናቄ አጀማመር

የሴቶች መብት ተከራካሪ የሴቶችን መብትና እኩልነት የሚያስጠብቅ ሲሆን በምዕራቡ እንዲሁም በመላዉ የአለም አቀፍ ህዝብ እና ድርጅቶች የሴቶችን መብት ለማስጠበቅ የተለያዩ እንቅስቃሴወችን ሲያደርጉ ይስተዋላል።

:-የመጀመርያዉ የእንስታዊነት መብት እንቅስቃሴ (ንቅናቄ) የተጀመረዉ ከ19 ኛዉ ክጳ ዘመን እስከ መጀመርያወቹ 20 ኛዉ ክጳ ዘመን ሲሆን የዚህ እንቅስቃሴ ሀሳብ የስራ ሁኔታ ፥ የትምህርት እድልና መብትን ነዉ።

ሁለተኛዉ የሴቶች መብት እንቅስቃሴ የተጀመረዉ በ1960 እስከ መጀመርያወቹ 1980 ሲሆን በዚህ እንቅስቃሴ የተነሱ ሀሳቦች የህግ እኩልነት አለመኖር ፥ የባህል እኩልነት አለመኖር ፥ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለ የሴቶች አስተዋፅኦ ነዉ።

ሶስተኛዉ የሴቶች መብት እንቅስቃሴ የተጀመረዉ በ1991 የሴቶች መብት ተሟጋች በሆነችዉ Rebecca Walker ሶስተኛዉ እንቅስቃሴ በሚል ባሳተመችዉ እትም የተለያዩ ክስተቶች

ተከስተዋል ። ከነዚህም መካከል በትምህርት ላይ ያሉ የፆታ እኩልነት እንዲሁም በ 1994 የሴቶች የመብት ጥሰቶች ናቸዉ።

አራተኛዉ የሴቶች መብት እንቅስቃሴ የተጀመረዉ በ2012 ሲሆን የማህበራዊ ሚዲያወችን ለምሳሌ ፡- ፌስቡክ ፣ ቲዉተር ፣ኢንስታግራም ፣ ዩቱዩብ ጋር በመተባበር አላማቸዉ በፍትህ የሴቶችን ጥቃት ፣ የሴቶችን ትንኮሳ እንዲሁም የሴቶች መብት ጥሰት ለመከላከል ተሰርቷል። ዋና ዋና ሀሳቦች መካከል በስራ ቦታ የሚደረጉ የሴቶች ትንኮሳ ፣በካፓስ ላይ የሚከሰቱ አስገድዶ መድፈር ናቸዉ። ( **ድረ ርእጅኝሽእ ርእንኝእን ፣ 2019 ፣ 120- 121)ቸ 2 ሸ**

# 2.5.የእንስታዊነት አይነቶች

## 2.5.1.ሊብራል እንስታዊነት

ሊብራል እንስታዊነት ሴቶች በማህበረሰቡ ዘንድም ሆነ በሌላ መልኩ ከወንዶች እኩል መብትና ነፃነት ሊኖራቸዉ ይገባል የሚል ንቅናቄ ነዉ። ወንድ እና ሴት እኩል እንደሆኑ የሚያሳይ እና ማንም ሴት እንደማነኛዉም ወንድ በነፃነት ነገሮችን ወደኋላ ሳትል በማድረግ ከወንዶች እኩል የመሆን መብት አላት የሚል ንቅናቄ ነዉ።

> ሊብራል እንስታዊነት ያራምዷቸዉ ከነበሩት አመለካከቶች መሀል ሴቶች በማልበረሰቡ ዘንድ የወንዱን ያህል ነፃነት ሊኖራቸዉ ይገባል። ***ó***ከመማህበራዊ ህግጋጋት ይልቅ በግላዊ አሚነልቦና የተመሠረተ ገደብ የለሽ ሰባዊ ነፃነት መስፈን ይኖርበታል***ó*** ወዘተ የሚሉ ይገኙበታል። ( ተክሉአስኳል ፣ **2007** ፣ **205** )

## 2.5.2. ራዲካል እንስታዊነት

ራዲካል እንስታዊነት ማለት የፆታ እኩልነትን የሚያሳይ ንቅናቄ ነዉ። ወንድ እና ሴት እኩል እንደሆኑ እና ማንም ሴት ባህል ፣ሀይማኖቷ ወይም የአኗኗር ዘይቤ አይፈቅደዉም ብላ ወደ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ሳትመለስ ማድረግ ያለባትን ነገር ከወንዶች እኩል በመሆን ማድረግ እንዳለባትና እኩልነትን የሚያሳይ ንቅናቄ ነዉ።

> እራዲካል እንስታዊነት ***ó***ወንድ እና ሴት እኩል ናቸዉ ***ó*** በሁለቱ እፆታ መሀል ያለዉ ልዩነት የጥምረት ሳይሆን የከረረ ቅራኔ ማሳያ ነዉ።***ó*** አባዊ ስርዐት መደቆስ አለበት በሚሉ መርሆች የሚመራ በመሆኑ ለወግ ጠባቂወች በአያሌዉ ፈታኝ እንደሚሆን

ከመሠረታቸዉ ጀምሮ የተገለፀላቸዉ ጉዳይ ነበር ። ራዲካል እንስታዊነት መልካም የፓለቲካ እንቅስቃሴ አድርገዉ በመቁጠር በርካታ ሴቶች የተቀላቀሉበት ቢሆኑም ብዙም ሳይቆዩ የእንቅስቃሴዉ አብዮታዊ ንድፈ ሀሳብ ከአልጠበቁት የሒወት መስመር ያላትማቸዉ ጀመር ። ( ተከሉ አስኳል ፣ **2007** ፣**206**)

## 2.5.3.ማርክሲዝም እንስታዊነት

ማርክሲዝም እንስታዊነት የመደብ ጭቆናን ወይም የታችኛዉና የላይኛዉ ክፍል በማለት የሚቃረን ንቅናቄ ነዉ ።

ማርክሲስት እንስታዊነት የመደብ ጭቆናን የሚቃረን እና የአንዱ ክፍል በሌላዉ ክፍል ድህዉና ሐብታም የአኗኗር ወይም የኢኮኖሚ ብዝበዛ ዋና ዋና ገፅታወች ናቸዉ ። በተለይም ካፒታሊዝምን ለማባረር የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ከግምት ዉስጥ በማስገባት እንደ ገለልተኛ የፓትራሪክ ወይም የአባዊነት እንዳይመሰረት የሚል ንቅናቄ ነዉ ። ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸዉ የበላይነት ከጉልበት በላይ የካፒታል የበላይነት ዉጤት ነዉ ። ( ሳልቫይ ዋልባይ ፣**1990** ፣**3 ቸ3ሽ**

ስለዚህ የማርክሲዝም ንቅናቄ ፅንሰ ሀሳብ ምንድን ነዉ:- የታችኛዉና የላይኛዉ መደብ ወይም በሴትና በወንዶች ላይ ያለዉን ልዩነት የሚጋፋና ሴቶች በወንዶች የበታች ተደርገዉ መታዬት እንደሌለባቸዉና ሀይማኖታዊ ወይም ኋላ ቀር አስተሳሰቦችን አስቀርቶ ሴቶች በተሠማሩበት የሙያ ዘርፍ እኩል ከወንዶች እኩል ክፍያ የማገኝትና ከወንዶች እኩል ሁነዉ መስራት አለባቸዉ ብሎ ያምናል ። ሴቶች በትዳር ሁነዉ ከባላቸዉ ለመለያዬት እኩል ንብረት ከማፍራት ቀተጨማሪም እኩል ንብረት የመካፈል መብት ጭምር አላቸዉ ።

## 2.5.4.ጀንደር እንስታዊነት

ጀንደር እንስታዊነት በ**1990**ዎቹ አጋማሽ ነበር በስፋት እንዲታወቅ የተደረገዉ። በምዕራቡ አለም ከ **1970**ዎቹ ጀምሮ የጀንደር አጀንዳ በትላልቅ የትምህርት ተቋማት በነበሩት የተወሰኑ ሊሒቃን ወይም ዩኒቨርስቲ እና ኮሌጅ ዉስጥ የመወያያ ረዕሰ ጉዳይ የነበረ ነዉ ። ። ጀንደር እንስታዊነት ወይም የፆታ እኩልነት በሴት እና በወንዶች መካከል በባዮሎጂ ሳይሆን በማህበራዊ ፣ በፖለቲ ካ ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የሚወሰን የአገዛዝ እና የመልሶ ማልማት ስረዓትን የሚያመለክት ፅንሰ ሀሳብ ነዉ። ( ተከሉ አስኳል **2007** ፣ **217**)

ጀንደር እንስታዊነት በፆታ ላይ መሰረት ያደረገ እና ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸዉ የሚል ንቅናቄ ነዉ ። የፆታ እኩልነትን የሚያሳይልን በሴቶች እና በወንዶች መካከል ከተፈጥሯዊ ነገሮች ዉጪ በማህበራዊ ፣ በኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ያሉት ነገሮች ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት እንዳላቸዉ ለማሳወቅ ያለመ ንቅናቄ ነዉ።

## 2.6. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት

አጥኝዋ ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ በምሰራበት ጊዜ የተለያዩ ስራወችን ዳሳለች። ነገር ግን ከጥናቱ ጋር የተሻለ ቅርበት ያላቸዉን በረካታ ፅሁፎችን ማግኘት ባትችልም ያገኘችዉ ጥናታዊ ጹሁፍ አንድነት እና ልዩነቱን ታቀርባለች ። እየሩሳሌም ሙሉጌታ በ 2013 ሰዉነቷ ፊልም ከገፀ-ባህርያት አሳሳል እና ከእንስታዊነት አንፃር በሚል ርዕስ ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርት ባልችለር ድግሪ ያቀረበችዉን ጥናታዊ ፅሁፍ ተመልከታለች ። በፊልሙ ዉስጥ ስላሉ ገፀ-ባህሪያት ከእንስታዊነት አንፃር የሚተነትን እና የሚያጠና በመሆኑ ከአጥኝዋ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር አንድነት እና ግንኙነት አለዉ ። ልዩነቱ ደግሞ ዋናዉ ጥናታዊ ፅሁፍ ከልብ - ወለድ አንፃር የሚተነትን ሲሆን ይህኛዉ ጥናታዊ ጹሁፍ ግን ፊልሙ ላይ ስለ ገፀ - ባህርያት አሳሳል አንፃር ይተነትናል።

ጌታነህ ደጉ በ 2011 በተመረጡ የአማረኛ ፊልሞች ላይ የአንስት ገፀ ባህርያት አሳሳል እና ከእንስታዊነት አንፃር በሚል ርዕስ ለጎንደር ዩኒቨርስቲ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርት ባልቺለር ድግሪ ማሟያ የአቀረበዉን ጥናታዊ ፅሁፍ ተመልከታለች። በፊልሙ ዉስጥ ስላሉ የአንስት ገፀ- ባህርያት ከእንስታዊነት አንፃር የሚተነትን እና የሚያጠና በመሆኑ ከአጥኝዋ ጥናታዊ ጹሁፍ ጋር አንድነት ሲኖረዉ ልዩነቱ ደግሞ ዋናዉ ጥናታዊ ፅሁፍ ልቦለድን የሚተነትን ሲሆን ይህኛዉ ጥናታዊ ፅሁፍ ግን ፊልም ላይ ስላሉ የአንሰት ገፀ- ባህርያት አሳሳል አንፃር ጭምር ይተነትናል።

# ምዕራፍ ሶስት

# 3.የመረጃ ትንተና

## 3.1.የጭን ቁስል ልቦለድ ታሪክ

ይህ የሒወት ታሪክ በዋናነት የሚያጠነጥነዉ በሰናይት የሒወት ታሪክ ላይ ነዉ። ታሪኩ የሚጀምረዉ ቀጨኔ ህፃናት ማሳደጊያ የአሁኗ አለኔ ግብርና ቴክኒክ ኮሌጅ ወደሆነዉ ህፃናት አንባ ማሳደጊያ የገባችዉ ነፍስ ሳታዉቅ ማለትም ገና የአራስ ልጅ እያለች ነበር ። ሰናይት ነፍስ እስካወቀችበት ጊዜ ድረስ በአንባ ዉስጥ ያሉ ህፃናት ወንድሞቿ እና እህቶቿ የቀድሞዉ የኢትዮጵያ መሪ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ሀይለማርያም ደግሞ የሁሉም አባት። ኢትዮጵያ ደግሞ የሁሉም እናት ይመስላሏት ነበር ። አንድ ቀን እንደተለመደዉ ትምህርት ሲዘጋ ወደ ቤተሰቦቻቸዉ ማለትም ለነሱ እንደናት እና እንዳባት ወደሆኑት ቤተሰቦቻቸዉ ይሔዳሉ ። ከሔዱ በኋላ ግን ሰናይት ቤተሰቦቿን እንደጠበቀቻቸዉ አላገኘቻቸዉም ። የእዉነት ቤተሰቦቿ የመሰሏት ሰዉች ሁሉ ፊት ነሷት። ከዚህ በፊት የነበረዉ አቀባበል አልነበረም የጠበቃት። እንደናት ሁና ያሳደገቻት ዙርያሽወርቅ ለሰናይት እናቷ እንዳልሆነች እና በጊዜ መጠጊያዋን እንድትፈልግ ነገረቻት። ነገሩን መቀበል ባትችልም መዉጣት እንዳለባትም ስለነገረቻት ቤቱን ትታ ትሔዳለች ። በኋላም ናዝሬት ከተማ ዉስጥ ከሚገኘዉ ማርያም በረተክርስቲያን አመራች ። ከዛም ለቀናቶች ከቆዩች በኋላ ወደ አዲስ አበባ ስራ አፈላልጋ የቤት ሰራተኝነት ትቀጠራለች ። መስከረም ሶስት ላይ ወደ አንባዉ ትምህርት ሲከፈት ተመለሱ ። ሰናይት ግን ከድሮዉ የበለጠ ህመምና ጭንቀት ይደራረብባት ጀመር በዚህ አጋጣሚም የአባዉ መምህራኖች ፣አስተዳደሮች እንዲሁም ሰራተኞች ሊረዷት አልቻሉም ። የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ ሰማንያ ዘጠኝ አመተ ምህረት ላይ አንባዉን ለቀዉ እንዲወጡ ተደረገ። ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አንባዉ ፈራረሰ። ቀጥታ ወደ ናዝሬት ወደምትገኘዉ ማርያም ቤተክርስቲያን አመራች። ለትንሽ ጊዚያት በዛ ቦታ ስትቆይ ግን ያሳለፈቻቸዉ ጊዚያት ሁሉ በጣም አስከፊ ነበር ። የጎዳና ተዳዳሪ ወንዶች መድፈር ሳይችሁ ሲቀሩ የተለያዩ የሰዉነት ክፍሎቿ ላይ ጉዳት ያደርሱባታል። በነዚህ ችግሮች ምክንያት ሒወቷን ለማጥፋት

ሙከራ ታደርጋለች ። አንባዉ ከፈረሰ በኋላ ያንባዉ ልጆች ተበታትነዉ ጎዳና ላይ በብዛት ሲኖሩ እንደነበር አሁን ላይ በተደጋጋሚ ኡኡታቸዉን አሰምተዉ ወደ አንባዉ እየተመለሱ መሆኑን ስታዉቅ ወደ አንባዉ ትመለሳለች ። ጭንቀቷና ህመሞ ሲበረታባት ከአንባዉ መዉጣት ስለፈለገች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አንባዉን ለቃ ለመሔድ ትሰናበታለች ። ከዛ ወደ ናዝሬት ቡና ቤት ዉስጥ ለመስራት አመራች። አንዳሰበችዉም ቡና ቤት መስራት ጀመረች። በስዓቱ ወንዶች እንዲነኳት ፈቃደኛ ስላልነበረች ወንዶች ይሰድቧት ጀመር። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ መቀጠል ስለማትችል በቀጣዩ ቀን አንድ ወንድ ከሆቴሉ ዉስጥ ያያትና ወደሱ ትሔዳለች። ከዛም እያወሩ በደንብ ይግባባሉ ለጊዜዉ እሱም ችግሯ ተሰምቶት ስራ ሊያስቀጥራት እንደሚችል እና ያለበትን ቦታ ነግሯትና ገንዘብ ሰጥቷት ተሰናብቷት ይሔዳል ። አንድ ቀን አዋሽ አርባ ወደሚገኘዉ የወታደሮች ካንፕ ከጓደኛዋ ጋር ትሔዳለች ። ቡና ቤት ዉስጥ ያገኘችዉን ፍቅሩ ሀይሉን አገኘችዉ። ከዛም ሲዝናኑ ከቆዩ በኋላ ወደ ማደርያ ክፍል ይሔዳሉ። ገብተዉ ትንሽ ከተጨዋወቱ በኋላ ፍቅሩ መጥፎ ባህሪ ማሳየት ጀመረ። አሁኑኑ ግንኙነት ማድረግ እንደሚፈልግ ጠዬቃትጵ ሰናይት ግን በሀሳቡ ስላትሰማማች ልታስረዳዉ ብትሞክርም እሱ ግን አንዴ ያሰበዉን ነገር ከማድረግ ወደኋላ ሳይል ድርጊቱን እንዲያቆም ስትማፀነዉ እሱ ግን የስድብ እና የብትር ናዳ እያወረደባት እግሯን ከአልጋዉ ብረት ጋር በማሰር ትንፍሽ እስኪያጥራት አድርጎ አስገድዶ ይደፍራታል ። ብትጮህም ምንም ሰዉ ሊደርስላት አልቻለም። ከዛ ሁሉም ነገር ካበቃ በኋላ አሁንም ለሁለተኛ ጊዜ መገናኘት እፈልጋለሁ ይላታልጵ የመናገር አቅምም ሆነ ጉልበት ስላልነበራት ለወሲብ ወይም ለግብረ ስጋ ግንኙነት አስፈላጊ ባልሆነ ቦታ ላይ ይደፍራታል ። በቀጣይ ቀን መንገዳደኗን ወደ ናዝሬት ማርያም ቤተክርስቲያን አመራች። በጎዳና ሒወት ኑሮዋን ቀጠለች። የተለያዩ ነገሮችን በማድረግ ጫት፣ ሲጋራ በመጠቀም እንዲሁም በልመና ላይ የጎዳና ሒወቷን ተያይዛዉ ለሁለት አመታት ዘለቀች ። ከለታት አንድ ቀን ግን የጎዳና ሒወት ሲሰለቻት ወደ ዝዋይ ሒዳ ስራ መስራት ጀመረች። በምትኖርበት አካባቢም ያሉ ጎረምሶች መግቢያ መዉጫ ያሳጧት ጀመር። ከዛም አንድ የቤቱ አከራይ የሆነ ቤቢ የሚባል ሰዉዬ በሰናይት ፍቅር ወደቀ። የፍቅር ጥያቄዉን ተቀብላ አብረዉ ተጋብተዉ መኖር ጀመሩ ። ከቀናት በኋላ ግን የቀድሞዉን ቤቢ እያጣችዉ መጣች ባህሪዉ ተለወጠ በገዛ እህቶቹ ሰናይት መሰቃዬት ጀመረች ። ብትነግረዉም ችግሯን ተረድቶ ሊያፅናናት ሲገባ ከነሱ የበለጠ በሱም መሠቃዬት ማቆም አልቻለችም ። ነገሮች ካቅም በላይ ሲሆኑባት ትዳሯን እና ቤቷን ጥላ ወደ አዲስ አበባ ሒዳ ቤት ተከራይታ ስራ እያፈላለገች ባለችበት ጊዜ ባለቤቷ ቤቢ እየተከታተለ አብራዉ መኖር እንድትችል ያስገድዳትና አብረዉ ከዛዉ መኖር ይጀምራሉ ። አብረዉ እዬኖሩ ባሉበት ጊዜ እንድታረግዝ ያደረጋታል። ካረገዘች በኋላ ልታስወረደዉ እንኳን በማችልበት ሁኔታ ትቷት ይጠፍል ። እሷም ፅንሱን ለማስወረድ በጊዜዉ ገንዘብ እንኳን ሳይኖራት የተለያዩ መድሀኒቶችን ተጠቅማ ለሒወቷ አስጊ ሁኖባት ነበር ። ምንም ነገር ስላልነበራት ስራ ስታጣ ያላት አማራጭ አሁንም ወደ ቡናቤት ሒወት መመለስ ነዉ ። ከተለያዩ ወንዶች ጋር መዉጣት

ወይም ማደር ትጀምራለች። ወንዶች እንደፍላጎታቸዉ ሳትሆንላቸዉ ሲፈልጉ ገንዘብ ሳይሰጧት እና ሲደበድቧት ይባስ ብሎም የራሷን ገንዘብ ጭምር በመዉሰድ በዛ ጨለማ ዉስጥ ያባርሯታል ። በዚም ሆነ በዛ ብላ ያገኘችዉን ገንዘብ ለቤት ክራይ ክፍያ ታዉላለች ። በዚህ ስራ መቀጠል ይባስ ብሎ በወንዶች የሚያደርሱባትን በደል ፣ ጫና መቋቋም ሲያቅጣት እዛዉ የስራ ማስታወቂያዎችን በማንበብ ስራ ማፈላለግ ጀመረች ያሰበችዉንም የስራ እድል አግኝታ የሽያጭ ማስታወቂያ የሚል ድርጅት ላይ ተቀጥራ መስራት ጀመረች ። ከዛም ከድሮ የተሻለ ሒወትን በነፃነት ቀጠለች። በዚህ ስራ ምክንያት ሒወቷን ካለስጋት መምራት እንድችል አድርጎታል ። በሌላ በኩል ደግሞ ከኪነ - ጥበቡ አለም መዉጣት ስለማትፈልግ የተለያዩ ፅሁፎችን እዩፃፈች ሒወቷን ከማንም ጥገኛ ሳትሆን እነዚህን ሁሉ ፈተናና ስቃይ ተቋቁማ ኑሮዋን አሻሽላ አሁን ላለችበት የተሻለ ሕይወት ደርሳለች።

## 3.2. የጭን ቁስል ልቦለድ ላይ ሴቶች በምን መልኩ ተስለዋል

ከዚህ ልቦለድ ታሪክ ላይ የምናገኛቸዉ ገፀ ባህርያት አብዛኛዉን ጊዜ የቡና ቤት ሰራተኞች እና የጎዳና ተዳዳሪ ሴቶች እንዲሁም ህፃናት ማሳደጊያ ዉስጥ የነበሩ ሲሆኑ ታሪኩን የሚያስቀጥሉልን ወይም በዚህ የጭን ቁስል ልቦለድ ላይ ባለታሪኳ የሆነችዉ ሴት ሰናይት ስትሆን ይች ባለታሪክ ህፃናት ማሳደጊያ ዉስጥ ያደገች፣ የተማረች የሚደርሱባትን ነገሮች ላይ ተቆቁማ በዛ ችግሮች ላይ ማለፍ የምትችል፣ ተስፋ የማትቀርጥ ፣ጠንካራ ሴት ናት። በሌላ መንገድ ዙሪያሽወርቅ የሰናይት አሳዳጊዋ ማለትም እንደናት ሁና ያሳደገቻትና ለዚህ ሁሉ ችግር ሰናይት እንድትጋለጥ ያደረገቻት ሴት ናት። በጭን ቁስል ልቦለድ ላይ የተሳሉት ገፀ ባህርያት ሴተኛ አዳሪ የሆኑ ገንዘብ በማጣት ምክንያት ወደዚህ ተግባር የተሰማሩ እና ለረጅም አመታት ጭምር ሲሰሩ የቆዩ ከችግራቸዉ ለመዉጣት ሲሉ ከተለያዩ ወንዶች ጋር በመዉጣት ክፍያ ማግኘት ሲሆን ወንዶች በፈለጉት ሰዓት ሴቶችን አግኝተዉ በገንዘባቸዉ መግዛት እና በዛዉ ልክ እደፈለጎቸዉ ይጠቀሟቸዋል። ከዚህ ባሻገር አብዛኛዉን ሴቶች ማለትም ቡና ቤት የሚሰሩ ራሳቸዉን ከዚህ ሒወት ለማዉጣት የማይችሉ ተስፍ የሌላቸዉ ናቸዉ። ዋናዋ ገፀባህሪ ግን ወደ ሴተኛ አዳሪነት የገባችዉ ራሷን ለመቻል ያላት ፍላጎት እና ከዛሬ ነገ የተሻለ ሒወት አገኛለሁ በማለት ነበር።

## 3.3.የጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ሴቶች ከእንስታዊነት አንፃር እንዴት ተገልፀዋልጵ

በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደተገለፀዉ እንስታዊነት ማለት ለሴቶች እኩልነት መብት የሚታገል ሲሆን ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ፣ ሞራላዊ እንዲሁም ህጋዊ እኩልነትን ለማስከበር እና ለመመስረት የሚታገል ንቅናቄ ነዉ። በዚህ የጭን ቁስል ልቦለድ ታሪክ ላይም አጥኝዋ ያገኘቻቸዉ ሴቶች በኢኮኖሚያዊ ፣ በማህበራዊ ፣ ፓለቲካዊ መብታቸዉን ተነፍገዉ ብዙ በደልና ግፍ ደርሶባቸዋል ። በዚህ ታሪክ ላይ ዋና ገፀ - ባህሪዋ ወይም

ሰናይት ከማህበረሰቡ በመገለል እና ወላጅ አልባ በመሆኗ ምክንያት በጎዳና ሒወቷ ላይ የነበረች እንዲሁም ከሰዉ ቤት ሰራተኝነት ተቀጥራ በምሰራበት ጊዜ ብዙ ስራዋችን ከማሰራት ባሻገር ከቤታቸዉ እንድትወጣ ያለደረገችዉን የስርቆት ተግባር አድርገሻል በማለትና የሰራችበትን ክፍያ ሳይሰጧት ሌባ ነሽ በማለት ሲያባርሯት ተመልክታለች። ይንንም የሚያሳይልን ገፅ 65 -66 በስፋት ያሳዩናል። በሌላ መልኩ ቡና ቤት በምሰራበት ወቅት እና ትዳር ይዛ በምትኖርበት ጊዜ ጭምር በማህበረሰቡም ሆነ ወንዶች በሴቶች ( በሰናይት ) ላይ የሚያደርሱትን ጫና ከእንስታዊነት ወይም ከሴትነት አንፃር ሙሉ በሙሉ ገልፆልናል ። ይህም ሲባል በታሪኩ ላይ እንደተመለከተችዉ ፡-ሰናይት ከማደጎ ሒወቷ ተነስታ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘችም ነበር። እንደ አስቸጋሪ ሰዉ ትታያለች ። በዛ ላይ እንደፍላጎቷ አትሆንም። ብቸኝነትን ፈልጋ ብቻዋን ለመሆን ባደረገችዉ ነገር እንደጥፋተኛ አይተዋት ይሰድቧት፣ ይደበድቧት፣ ይጮኹባት ነበር ። ይሔን ተግባር ገፅ 25 እና 26 ያሳይልናል።

ሞግዚት ፡-( በጩኸት ) **ዕ** የት ሄደሽ ነዉ አንቺ**ጵ** **ዕ**

ሰናይት ፡- **ዕ** እ....ኔ...እንቅልፍ እንቢ ብሎኝ...

ሞግዚት ፡- እኮ ምናባሽ ቢቆርጥሽ**ጵ**

አባባ ከበደ ፡- ነግሬሻለሁ ሙሉ ጎጃም... ይሔ ብቸኝነት መዉደድ ፣አልመገብም ማለትና እዛ ቆሻሻ ቦታ መሄድ ቢቀርብሽ ይሻላል።**ዕ**( በመደብደብ)

ሰናይት ፡- ዝም ብዬ አለቅሳለሁ

አባባ ከበደ ፡- **ዕ** ሰምተሸኛል ነምልሽን**ጵ** **ዕ**

ሰናይት ፡- አዎ ስል እራሴን እነቀንቃለሁ።

ከታሪኩ ላይ በሌላ መልኩ እንደሚያሳየዉ ከአሳዳጊዋ እናቷ ዙርያሽወርቅ የትም መሔድ እንደማትችል እያወቀች በምናገባኝነት ስሜት ከቤቷ አሰወጥታለች። ተጨማሪም በህፃናት ማሳደጊያ ዉስጥ ያሉ ሰራቸኞች ለሷ ጥሩ አመለካከት አልነበራቸዉም። ከነሱ ጋር በምትገናኝበት ሰዓት አስቸጋሪ ሰዉ እንደሆነች ሆን ብላ እንደምታስቸግር በተደጋጋሚ እየተቃወሙ ይነግሯት ነበር። ከማሳደገመያ ከወጣች በኋላም በጎዳና ሒወት ላይ ያሳለፈችዉ በወንዶች የመድፈር ሙከራና እስከመደብደብ እንዲሁም በአካል ክፍሎቿ ላይም የተለያዩ ጉዳቶችን ሲደርስባት እንዲሁም ከማነቋሸሽ በተጨማሪ የተለያዩ ስድቦችን ይሰድቧታል ፣ ያስፈራሯታል ፣ አላስፈላጊ ቃላቶችን ጨምር ይናገሯታል። ይሔንንም በይበልጥ የሚያሳይልን ገፅ 90 ላይ ነዉ።

አንደኛዉ ጎረምሳ ፡- ዛሬ ከኔ ጋር ብታድሪ መሬቱን ሁሉ ለግዛትሽ እሰጠሽ ነበር !

ሁለተኛዉ ጎረምሳ ፡- ባርቾ... ነፍሴ... ብርድ ልብሴ... ልተኛሽ አድርጌሽ ትራሴ!

ሶስተኛዉ ጎረምሳ ፡- ኩራቷ ደሞ.... ብጣሻም!

አራተኛዉ ጎረምሳ ፡- እረ በናታችሁ ትንሽ ቀን ጠብቋት ኩራቷ ሞቷ ይሆናል....

በቡና ቤት ሒወቷም ታሪኩ እንደሚያሳዬዉ አንድ አይነት ድርጊቶች ነበር በወንዶች ጥቃት የሚደርስባት ። ወንዶች ሴቶችን የራሳቸዉ ንብረት እስኪመስሏቸዉ ድረስ በገዛ ገንዘባቸዉ እንደቃ እየገዙ የሚጠቀሚቸዉ እንደሆኑ እያሰቡ በራሳቸዉ መንገድ እያዘዙ ከትዛዛዉ ዉጪ ሲሆኑ በማስገደድና ገንዘባቸዉንም ጭምር ሳይሰጧቸዉ በደብደብ እና በማንቋሸሽ ያስወጧቸዋል። ይሔን በስፋት የሚያሳይልን ገፅ **250-252** እና ከ **260-264**።

በሌላ መልኩ ደግሞ ትዳር ይዛ በምትኖርበት ሰዓት ከማህበረሰቡ ባሻገር በባለቤቷ ዘንድ በደል ደርሶባታል ተቀባይነትም አላገኘችም ። በገዛ በባለቤቷ እህቶች ምክንያት የተለያዩ ስነልቦናን የሚጎዱ ስድቦች ይደርሱባታል ። በአጠቃላይ በገፀ - ባህሪዋ በሰናይት ላይ በኢኮኖሚያዊ ፣ በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ መብቷን ተቀምታ እና ሞራላዊ ጭምር የሆነ ብዙ በደልና ግፍ ስቃይ ሲደርስባት ያሳያል። የዚህ ድርጊት ማሳያ ገፅ **142 - 147** ። ከዛ በተጨማርም ሴቶች ወይም ሰናይት ቡና ቤት በሚሰሩበት ጊዜ የሚደረስባቸዉ ነገሮች ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ወንዶች ለራሳቸዉ ሲሉ እና የወሲብ ስሜታቸዉን ለማነሳሳት ሲሉ ሴቶችን ያለምንም እርህራሔ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ይልቅ ሴቶችን እየደበደቡ ለስሜታቸዉ መወጫ ያደርጎቸዋል። ይሔን በይበልጥ የሚያሳይልን ገፅ **254** ላይ ተገልፃል። ከዚህ በተጨማሪ ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱት ጫና በሴቶች የጤና እክል ወይም የጤና ችግር ከማድረሳቸዉ ባሻገር ስነ -ልቦናዊ ጉዳትና የአካል ጉዳትን ጭምር ያስከትላል።

## 3. 4. የጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ሴቶች የሚደርስባቸዉ ጫና ምን ይመስላል፦

የጭን ቁስል ልቦለድ ታሪክ በእዉኑ አለም ያለ የገሀዱን አለም የሚያሳየን እየሆነ ያለዉን እና አሁን ላይ የተፈጠረዉን እዉነተኛ ታሪክ ያሳያል። ይህም ታርክ አሳዳጊ የሌላቸዉ ወይም ወላጅ አልባ ሁነዉ በጎዳና ላይ ላሉ እንዲሁም ሴት የጎና ተዳዳሪ ( ሰናይት) ላይ የሚደርሰዉ ጫና ወንድ የጎዳና ተዳዳሪወች በሴቶች ላይ የተለያዩ ስድቦችን አንዲሁም መደብደብና የመድፈር ሙከራ ያደርጋሉ። ወንዶች የጎዳና ልጆች በሴቶች ጎዳና

ተዳዳሪዎች ላይ ጫና፣ በደልን ፣ ያካል ጉዳትን ጭምር ያደርሳሉ ። በጭን ቁስል ልቦለድ ላይ እንደሚያመለክተዉ። ገፅ 96 ላይ እንዲሁም 97 ላይ በስፍት ይገለፃል።

አንደኛዉ ጎረምሳ :- ለመሆኑ አንች ከማን በልጠሽ ነዉ ጵ

ሰናይት :-ከማንም! ጫፌን ግን አትነኳትምጵ

ሌላኛዉ ጎረምሳ :- ወደሽ ነዉ በግድሽ የምትሰጭን ጵ

በሌላ መልኩ ደግሞ ሴቶች ወይም ሰናይት የቡና ቤት ስራ በሚሰሩበት ጊዜ ወንዶች እንደፈቃዳቸዉ ሳይሆኑ ሲቀሩ መሳደብ፣ መዝለፍ ይፈልጋሉ ። በሌላ በኩል ወንዶች ሴቶችን በማታለል እና ስራ አስቀጥርሻለሁ በሚል ተልከሻ ምክንያት ሴትን ልጅ ያለ አግባብ ስም በመስጠትና ገና ለገና አልባሌ ወይም የማይሆን ቦታ ወስጥ ስለተገኘች በተግባሩ ተሰማርታለች ብሎ በማሰብ ( ሰናይት) ወስዶ በማታለል በሴቶች ደካማ ጎን ተጠቅመዉ ከሰናይት ላይ የመድፈር እንዲሁም ለወሲብ ተፈጥሮአዊ ባልሆነ ቦታ በመጠቀምና በመስደብ ፣ በመደባደብ ፣ በማንቋሸሽ እና የጤና ችግር ጭምር እንዲያጋጥማት በወንዶች በደል እና ጫና ምክንያት ሒወቷ ተስፍ እንዲያጣ ሆናለች ። ይሔን የሚያሳይልን ገፅ 142 - 147 ላይ ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ጫና እንመለከታለን ።

ፍቅሩ :- ሴክስ እንድናደርግ እፈልጋለሁ

ሰናይት :- ኖ ፍቅሩ እኔ ድንግል ነኝ

ፍቅሩ :- እረ ባክሽ ( በሹፈት )

ሰናይት :- ሙት..... በናትህ እኔ አምኜህ ነዉ ዝም ብዬ የተቀመጥሁት

ፍቅሩ :- የማላቅሽ መሰለሽ ጵ ሸርሙጣ ! ቡና ቤት አይደል ያገኘሁሽ

ሰናይት :- እና .. ቢሆንስ ...... ልግባ አልግባ እያልኩ እዬታገልኩ እያለ አግኝቼህ ተስፍ ስለሰጠኸኝ አይደል ትቸዉ የመጣሁት

ፍቅሩ :- በጣም ጥሩ ። ስራዉን አስቀጥርሻለሁ ብዬሻለሁ ። አንቺ ደግሞ ልትችገሪልኝ ይገባል ።

ይሔን በማለት ወንዶች በሴቶች ላይ ደካማ ጎናቸዉን በመጠቀም እና ይሔን ላድርግልሽ አይደል አንችም በተራሽ ይሔን ማድረግ አለብሽ በማለት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ወንዶች

በሴቶች ላይ ፍላጎታቸዉ እስኪሟላ ድረስ የመስደብ ፣ የማንቋሸሽ እና የመድፈር ጭምር ጥቃት ያደርሳሉ ። በሌላ መልኩ ደግሞ የቡና ቤት ሴቶች ላይ የሚደርሰዉ ጫና ሲታይ ከወንዶች ጋር በሚወጡበት ጊዜ እንደፈቃዳቸዉ ሳይሆኑ ሲቀሩ መሳደብና መዝለፍ ይፈልጋሉ አብዛኛዉን ወንዶች ደግሞ ሴቶችን ወይም ሰናይትን ወንዶች እቃ እንደሚገዉ አንዲት ሴት አብራዉ አሰንድታድር በዋጋ ተስማምተዉ ከወሰዱ በኋላ የሰሩትን ብር አለመስጠት እንዲሁም አብሶ መደብደብ በሌላ በኩል ደግሞ የራሳቸዉን የሴቶችን ገንዘብ ጭምር ይወስዳሉ። በጨለማ ዉስጥ አስወጥተዉ ለታክሲ እንኳን እስኪያጡ ድረስ ለምነዉ ወደ ሚሔዱበት እንዲሔዱ ይደረጋሉ። በዛ ላይም የተለያዩ ችግሮች በመንገድ ላይ ያጋጥማቸዋል። ይሔን የሚገልፅልን ገፅ **254 - 256** ያሳይልናል። በሌላ በኩል ወንዶች በሴቶች ላይ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ፖለቲካዊ እንዲሁም ሞራላዊ ጫናወችን ያደርሳሉ።

- ማህበራዊ ፡- በማህበራዊ ዘንድ የሚያመለክተዉ በአገራችን ብዙ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ሴቶች ማህበራዊ ጫና ሲደርስባቸዉ እንመለከታለን። ይሔም ሲባል ገፀ - ባህሪዋ ሰናይት በአደገችበት አንባ ስር መንግስትም ሆነ የመንግስት ተቋማት እንዲሁም በአንባዉ ስር ያሉ የህፃናት አሳዳጊወች ሀላፊነት ስላልተሰማቸዉ ከአንባዉ ዉስጥ የኖሩ ልጆችን በማናለብኝነት ያስወጣሉ። በተጨማሪም ሰናይት እንደናት ሁና ያሳደገቻት ሴት ዙርያሽወርቅ የት ትደርሳለች ሳትል በጊዜ መጠጊያዋንና መኖርያዋን እንድትፈልግ ከቤት አስወጥታታለች። ገፅ **50 - 56** ይሔን በስፋት ይገልፅልናል።

ዙርያሽወርቅ ፡- ( ትንፋሿ እዬተቆራረጠ ) እናትሽ አደለሁም ! በጊዜ መጠጊያሽን ፈልጊ

ሰናይት ፡- ( ከግሯ ወድቃ እያለቀሰች ) ዙሪያሽዬ በእናትሽ! ያጠፋሁት ካለ ይቅር በይኝ... ይህችን ክረምት ብቻ እንኳን ልቆይ**ጵ** ስሞትልሽ ሁለተኛ ድርሽ አልልም...... ይህችን ክረምት ብቻ!

በሌላ በኩል ትዳር ይዛ በምትኖርበት ሰዓት የባለቤቷ እህቶች ይሰድቧታል። ትዳሯን እንድትተዉ እና ከወንድማቸዉ ጋር ያላትን ግንኙነት እንድታቋም በሌላ ሰወች አማካኝነት እዬደጋገሙ ዛቻና ማስፈራሪያ ያደርሱባታል። ሒይወቷን መቀጠል እንዳትችል አድርጎታል። ይሔንንም የሚያመለክተን ገፅ **198** ላይ ነዉ።

- ፖለቲካዊ ፡- ይህ የጭን ቁስል ልቦለድ ፖለቲካን የሚያመለክተዉ የችግሮች ሁሉ ተጠቂ ሴቶች መሆናቸዉን ተከትሎ ወንዶች የበላይ ነን በማለትና ሴት በወንድ ስር ናት በሚል ደካማ አስተሳሰብ ምንም አታመጣም በማለት ሀሳብ የሚያደርሱት ፖለቲካዊ ጫና ነዉ። በሌላ በኩል ወንዶች ስልጣንን ገደብ በማድረግ እንደፈቃዳቸዉ ካልሆኑ አንድን ሴት በመሳደብና በማስፈራራት ጉዳት ያደርሱባቸዋል። ገፅ **116 - 118** ላይ ወንዶች ስልጣናቸዉን ወይም የተሰማሩበትን የስራ

ዘርፋ ገደብ በማድረግ ሴቶችን በመሳደብ እና አላግባብ ጥያቄዎችን በመጠዬቅ ሴቶች ላይ ጭንቀትና ፍርሀትን ጭምር ይፈጥራሉ።

አበበ ፡- ለምን ቃልሽን አትሰጭም

ሰናይት ፡- ነገ ጥዋት እሰጣለሁ

አበበ፡- ነይ ዉጪ

ሰናይት ፡- እንዴት በዚህ ስአት ቃል እሰጣለሁ፧

አበበ ፡- ወንጀለኛ ቃል ለመስጠት ጊዜ መምረጥ አይችልም

ሰናይት ፡- ወንጀለኛ አይደለሁም።

አበበ ፡- በመሰረቱ ነሽ! እኔ ግን ወንጀለኛ እንዳይደለሽ አድርጌ ላስወጣሽ እችላለሁ።

ይሔን በማስመልከት አንዳንድ ወንዶች ስልጣናቸዉን ገደብ አድርገዉ በሴት ልጅ ላይ ጭንቀት እና በደልን ያደርሳሉ።

- ኢኮኖሚያዊ ፡- ይህ ታሪክ ዋናዉ ሀሳቡ እንስታዊነት ወይም ከሴቶች ጫና ከመሆኑ ባሻገር በኢኮኖሚ ማጣት ምክንያት ማለትም ገንዘብ በማጣት ምክንያት የአገራችን ሴቶች በወንዶች የበታች እንዲሆኑ አድርጎል። ይህ ልቦለድ እንደሚያሳዬዉ ምጣኔ ሀብታዊ ነገሮችን በማጣት ምክንያት ሴቶች የተለያዩ ስራዎችን ከመስራት ወደ ኋላ አይሉም። ሰናይትም ያጋጠማት ችግር ይሔ ነበር። የራሷ ነገርም ሆነ ምትተዳደርበት ነገር ስላልነበራት ወደ ሴተኛ አዳሪነት ሒወት ተሰማርታለች። በዚህ ስራዋ ላይም ብዙ ዉጣ ዉረድን ከማሳለፍ በተጨማሪ ሴትነቷን ጭምር ማጣትና የጤና ችግርም አጋጥሞታል። በወንዶች ተገዳ ተደፍራለች እንዲሁም በጎዳና ላይ የሚተዳደሩ ወንዶች የአካል ጉዳትን አድርሰዉባታል። በተለያዩ የሰዉነት ክፍሎቿ ላይ በጩቤ ወግተዋታል። ይሔንንም የሚያሳይልን ገፅ **96** እና **97** በስፋት ያሳያል።

በቡና ቤት ሒወቷ ገንዘብን ለማግኘት ስትል ከተለያዩ ወንዶች ጋር በምትወጣበት ሰዓት የተለያዩ ችግሮችና የመደብደብ ፣ የማንቋሸሽ እንዲሁም የጤና ችግር እስኪያጋጥማት ድረስ ገንዘብን ለማግኘት ስትል ብዙ ችግር ደርሶባታል። በሌላ መልኩ ሴቶች በኢኮኖሚ ወይም በገንዘብ ማጣት ምክንያት ፈልገዉም ሆነ ሳይፈልጉ ወደ ትዳር አለም ይገባሉ የተሻለ ሒወት እንዲኖራቸዉ። ከጎዳና ወጣ እንድትኖር ገንዘብን መሰረት በማድረግና ሒወቷን ለማቆዬት ስትል በልመና ላይ ጭምር ተሰማርታለች። በሴተኛ አዳሪነት ሒወትም ከተለያዩ ወንዶች ጋር እንድትወጣ ሁናለች። ወንዶችም ይሔን መሠረት በማድረግ ማንም ሴት ቸግሯቸዉ ወደ ቡና ቤት ሒወት

እንደሚገቡ ስለሚያዉቁ በገንዘባቸዉ መግዛት ይጀምራሉ። ይሔም ሲሆን ኢኮኖሚ ከማጣት ባሻገር በተለያዩ በብዙ አካላዊም ሆነ የሥነ ልቦና መንቆሸሽ ጭምር ያጋጥማቸዋል

- ሞራላዊ ( ስነ - አዕምሮአዊ ) ይህ ድርጊት ስነ - አዕምሮአዊ በሴቶች ወይም በሰናይት ላይ ትልቅ ተፅኖ አለዉ። የጭን ቁስል ልቦለድ ታሪክ ላይ ገፀ - ባህሪዋ ሰናይት በወንዶች ያ ሁሉ ድርጊት ሲፈፀምባት ሞራላዊ ጉዳትም ደርሶባታል። ለምሳሌ ፦ ሒወቷን ለመምራት ስትፈልግ ገንዘብ በማጣት ምክንያት ገንዘብ ለማግኘት ስትፈልግ ወንዶች ብዙ ጉዳትን አድርሰዉባታል። በጎዳና ሒወቷ ፣ በቡናቤት ሒወቷ እንዲሁም በትዳር ሒወቷ ላይ በማህበረሰቡ ዘንድ ትዳር ይዛ በምትኖርበት ጊዜ የባሏ ታናሽ እህቶች ቤቱን ጥላ እንድትሔድ እና ያላትን ግንኙነት ጭምር እንድታቆም እና ትዳሯን ትታ እንድትሔድ አድርገዋታል። ይሔን የሚያሳይልን ገፅ **190-198** ላይ ይበልጥ ያሳይልናል። እንዲሁም በቡናቤት ሒወት ዉሴጥ በምትሰራበት ጊዜ ወንዶች በገንዘባቸዉ እስከገዟቸዉ ድረስ የፈለጉትን የማድረግና የተለያዩ ስድቦችን የመሳደብ የሴተኛ አዳሪነት ሒወትን ፈልገዉ እንደገቡ በማሰብ እንጅ በማህበረሰቡ ወይም በራሳቸዉ በወንዶች ምክንያት እንዲሁም የራሳቸዉን ሒወት ለማስቀጠል ሲሉ ወደዚህ ሒወት እንደገቡ አይገነዘቡም። ወንዶች ገንዘብ እካላቸዉ ድረስ ለሴቶች ሞራል ምንም ያክል ክብር የላቸዉም።

## 3.5. የጭን ቁስል ልቦለድ ዉስጥ ያሉ ሴት ገፀ -ባህርያት

## ከሊብራል እንስታዊነት ጽንሰ ሃሳብ አንፃርጵ

በምዕራፍ ሁለት እንደተገለፀዉ የተለያዩ የእንስታዊነት አይነቶች ተዘርዝረዋል ነገር ግን ይህ ጥናት የጭን ቁስል ልቦለድን ከሊብራል እንስታዊነት ፅንሰ ሀሳብ አንፃር ብቻ የሚተነትን ይሆናል። ሊብራል እንስታዊነት የሚያተኩረዉ ሴቶች እንደወንዶች እኩል መሳተፍ እና በትምህርት እኩል እድል የማግኘት ፣ በስራ ተመሳሳይ መብት የማግኘት ፣እኩል ደሞዝና ክፍያ የማግኘት እና ለሴቶች እንዲሁም ለግለሰቦች መብት እንዲከበር የሚደረግ ንቅናቄ ስለሆነ ነዉ። በዚህ ልቦለድ ታሪክ ላይ እንደሚያሳዬዉ የሴቶችን የበደል እና የጭቆና አይነት ያሳዬናል። ወንዶች ሴቶችን ለወሲብ ማርኪያ ሲያደርጓቸዉ ሴቶች የሚፈልጉትን ሳይሆን የሚታዘዙትን ብቻ እንዲፈፅሙ የማስገደድ ይሔን ተግባር ሳይፈፅሙ ሲቀሩ ደግሞ የማስገደድ ፣ የመስደብ ፣ የመደብደብ ፣ የሰሩበትን ገንዘብ የመከልከል እና የራሳቸዉን ገንዘብ ጭምር የመዉሰድ እንዲሁም የማንቋሸሽ ጫናዎችን ያደርሳሉ። በዚህም ምክንያት ሴቶች የአካል ጉዳት ፣ የአእምሮ መቃወስ በሌላ በኩል ደግሞ እራሳቸዉን ለማጥፋት ሙከራ ሲያደርጉ የተለያዩ በደሎች እንዲደርስባቸዉ ሲያደርጉ ያሳዬናል። ሊብራል እንስታዊነትም እንደዚህ አይነት ጭቆናና በደልን በማስወገድ ሴቶች በማነኛዉም ተሳትፎ ላይ በነፃነት ፣ በራሳቸዉ አመለካከትና ዉሳኔ መሳተፍ እንዲችሉ ሴቶች ከወንዶች እኩል መብት አላቸዉ የሚል ንቅናቄ ነዉ።

# ምዕራፍ አራት

# 4. ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሀሳብ

## 4.1.ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የጭን ቁስል የተሰኘዉ ልቦለድ ሴት ገፀ -ባህሪያት ከንስታዊነት አንፃር ቅኝት አድርጎል ። ይህ ልቦለድ የሚያነሳቸዉታሪኮች ከእዉነተኛታሪክ የተመሠረተ ከመሆኑም ባሻገር ለማህበረሰቡ የሚያስተላልፈዉ ዋነኛ መልዕክት ወንዶች በሴቶች ላይ ጥቃት የሚያደርሱባቸዉን ጫና እና በደል ከእንስታዊነት አንፃር ያሳያል ። ሰናይት ገና ያራስ ልጅ እያለች ነበር ህፃናት አንባ ዉስጥ የገባችዉ ። ካደገች በኋላ ግን ቤተሰብ አለመኖርን ስታዉቅ ማህበረሰቡም ለሷ ያላቸዉ አመለካከት ሲቀዬርበወንዶች የተለያዩ ጉዳቶች እንዲሁም አስገድደዉ እስከመድፈር ድረስ እነዚህ ችግሮች ከእንስታዊነት አንፃር ለማየት ተሞክሯል ። በዚህ ምክንያት በአገኘችዉ ስራ ላይ ተሰማርታለች። የቤት ሰራተኝነት ፣ ሴተኛ አዳሪነት ፣ እንዲሁም ነገሮች ሳይስተካከሉ ሲቀር ጎዳና ተዳዳሪ ሆናለች። የተሻለ ሒወትን ለማግኘት ሚስት በመሆን በነዚህ ዉጣ ዉረዶች መሀል በማህበረሰቡ ዘንድ መገፋትን በወንዶች ዘንድ በማነኛዉም ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ እንዲሁም ስነ አዕምሮአዊ ጫና ሲደርስባት ከእስታዊነት አንፃር ተዘርዝሯል። የጭን ቁስል ልቦለድ እንደተረዳነዉ ወላጅ አልባ የሆኑ የማደጎ ሴት ህፃናት ቤተሰቦቻቸዉን ባለማወቅ ምክንያት ቤተሰቦቻቸዉም ልጆቻቸዉን ባለመፈለግ ምክንያት ምን ያህል ስቃይ በደል ጭቆናና ህመም እንደሚደርስባቸዉ ከእንስታዊነት አንፃር ተጠቁሟል። ይህን ሁሉ ስቃይና መከራ የደረሰባት ሰናይት በወንዶች ምክንያትና ቤተሰብ በማጣቷ ምክንያት ሒወቷን በተደጋጋሚ ለማጥፍት ስትሞክር እና በወንዶች ብዙ ችግር ሲደርስባት ከእንስታዊነት አንፃር ተዘርዝሯል። በመጨረሻም ከእንስታዊነት አንፃር ወንዶች ከሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ጫና እና ችግር በጭን ቁስል ታሪክ ላይ በዝርዝር

ታይቷል። በመጨረሻም ሰናይት ይህን ሁሉ ችግርና ስቃይ ተቋቁማ ጥሩ ደረጃ መድረሷን እና ሴቶች ከወንዶች እኩል እንደሆኑ አሳይታለች።

## 4.2.የመፍትሔ ሀሳብ

አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ፁሁፍ የጭን ቁስል ልቦለድን በምታጠናበት ወቅት በልቦለዱ ላይ ከእንስታዊነት ፅንሰሃሳብ አንፃር ጥቂት መመልከት ችላለች።በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች ሊቀርፉ ይችላሉ ብላ እንደ መፍትሔ ሀሳብ ያነሳቻቸዉ ሀሳቦችን እንደሚከተለዉ ታቀርባለች።

- ወንዶች በሴቶች ላይ የሚያደርሱትን ጫና ለማስቆምሁሉም ሴቶች መስራት አለባቸዉ ብላ ታምናለች ።
- መንግስትም ሆነ ህብረተሰቡ ወላጅ አልባ በሆኑ ህፃናት እና በሴቶች ላይ መስራት ይኖርባቸዋል ።
- ማህበረሰቡ ለሴቶች ልዩ ቦታና ክብር እንዲሰጧቸዉ ግንዛብ መስጠት ወይም ማስተማር።
- ሴቶች ችግር ሲደርስባቸዉ ወደ ማህበረሰቡ ይበልጥ ደግሞ ወደ ህግ አካል በመሔድና በማጋለጥ መስራት ይኖርባቸዋል ።

# ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸዉ

1. ፍጠመኘነኘሰመ ኘሰ አ ነዐበለጠ ሠዐነሠጠፐተ አገአኘነሰተ ኘገነዐበለጠ ተሐዐሀገሐተ ዐፊ ደኘሰሠረኘመኘነአተኘዐነ ዐነ ተሐጠ ገረዐሀነደሰ ዐፊ ሰጠጨ.አተ ተሐጠ ዐሀተሰጠተ, ተሐጠ ደኘሸኘሰኘዐነጠ ዐፊ ገጠነደጠረ ረዐለጠሰ ወአሰ በአሰጠደጠ ዐነ ተሐጠ ሠአፐአሠኘተየ ተዐ በጠአረ አነደ ነዐሀረኘሰሐ ተሐጠ በአበኘጠሰ አነደተዐ ከጠጠፐ ፐረዐሸኘሰኘዐነሰ ረጠአደየ ኘነ ተሐጠ ጠነተኘረጠ ተኘመጠ ሰፐአነ. ትሐጠ ደኘሸኘሰኘዐነ ሐአደ ነዐ አረኀመጠነተሰ ፊዐረ ተሐዐሀሰአነደሰ ዐፊ የጠአረሰጸ በሀተ ወአሰ ለአተጠረ ዐነ ሠሐአለለጠነገጠደ ሰዐመጠተኘመጠሰ ለኘገሐተለየ አነደ ሰዐመጠተኘመጠሰ ኘነተጠነሰጠለየ. ትሐኘሰ መአየ በጠ ደሀጠ ተዐ መጠነ ተአከኘነገ ተሐጠረኘ ረዐለጠሰ መዐረጠ ሰጠረኘዐሀሰለየ አነደ ሀነደጠረመኘነኘነገ ፊጠመአለጠ ረዐለጠሰ ዐረ ነጠገአተኘነገ ተሐጠመ ሠዐመፐለጠተጠለየ ኘነ ተሐጠ ወሐዐለጠ ፐረዐገረጠሰሰኘዐነ ዐፊ ጠጨኘሰተጠነሠጠ. ምጠነፀሰ ፐሐየሰኘሠአለ ሰተረጠነገተሐ, ተሐጠረኘ አበኘለኘተየ ተዐ ሐሀነተ ( ኘነ መዐደጠረነ ተኘመጠሰ ተሐጠረኘ መዐነጠየ መአከኘነገ ሰከኘለለሰ) አነደ ፊረጠጠደዐመ ፊረዐመ ሠሐኘለደ በጠአረኘነገ ለኘአበኘለኘተኘጠሰ መአደጠ ተሐጠመ ሐኘገሐ ሐጠአደጠደ አነደ አረረዐነገአነተ ተዐወአረደሰ ፊጠመአለጠ.ሀነደጠረ ተሐኘሰ በአሠከደረዐፐ ወጠ ሠአነ ሰጠጠ ተሐጠ ሠረጠአተኘዐነ ዐፊ ፐአተረኘአረሠሐአለ ሰዐሠኘጠተየ ኘነ ወሐኘሠሐ አለለ ሰዐሠኘአለ ነዐረመሰ ወጠረጠ ሠረጠአተጠደ አነደ ሠዐነተረዐለለጠደ በየ መጠነ, መአከኘነገ ወዐመጠነ አ ፐአሰሰኘሸጠ ፐአረተነጠረ ኘነ ተሐጠ ወሐዐለጠ ሠዐሀረሰጠ. ፍጠመኘነኘሰመ ኘሰ ተሐጠ አደሸዐሠአሠየ ዐፊ ወዐመጠነፀሰ ረኘገሐተሰ ዐነ ተሐጠ ገረዐሀነደሰ ዐፊ ጠቀሀአለኘተየ ዐፊ ሰጠጨጠሰ. ኘተ ኘነኘተኘአተጠደ ኘነ ተሐጠ ወጠሰተ, ጠጨሐኘበኘተጠደ ተሐረዐሀገሐዐሀተ ተሐጠ ወዐረለደ አነደ ወአሰ ጠጨጠመፐለኘፊኘጠደ በየ ሠዐሀነተለጠሰሰ ፐጠዐፐለጠ አነደ ኘነሰተኘተሀተኘዐነሰ ሠዐመመኘተተጠደ ተዐ አሠተኘዐነ ዐነ በጠለኘጠፊ ዐፊ ወዐመጠነፀሰ ረኘገሐተሰ አነደ ኘነተጠረጠሰተሰ. ኘተ ሠዐሀለደ በጠ ተረአሠጠደ ወአየ በአሠከ ኘነ 3ረደ ሠጠነተሀረየ ብ᎔ጥ, ወሐጠነ ፀርዐመአነ ወዐመጠነ ፊኘለለጠደ ሠአፐኘተዐለኘነጠ ሐኘለለ አነደ በለዐሠከጠደ ጠሸጠረየ ጠነተረአነሠጠ ተዐ ተሐጠ ፊዐረሀመ በጠሠአሀሰጠ ሠዐነሰሀለ ሠአተዐ ረጠሰኘሰተጠደ አተተጠመፐተሰ ተዐ ረጠፐጠደለ ለአወሰ ለኘመኘተኘነገ ወዐመጠነፀሰ ሀሰጠ ዐፊ ጠጨፐጠነሰኘሸጠ ገዐዐደሰ ፀ.ሐዐወጠሸጠረ, ኘተሰ መዐደጠረነ

አሸአተአረ ሠአመጠ ኘነ ደኘፌፌጠረጠነተ ወአሸጠሰ በረኘነገኘነገ ፌዐረወአረደ ደኘፌፌጠረጠነተ አሰፐጠሠተሰ ዐፌ ፌጠመኘነኘሰተ ኘሰሰሀጠሰ.

2. ትሐጠ ፌኘረሰተ ወአሸጠ ዐፌ ፌጠመኘነኘሰመ ወአሰ ፌረዐመ 19ተሐ ተዐ ጠአረለየ 20ተሐ ሠጠነተሀረየ አነደ ኘሰሰሀጠሰ ረአኘሰጠደ ደሀረኘነገ ተሐኘሰ ፐጠረኘዐደ ወአረጠ ሰሀፌፌረአገጠ, ወዐረከኘነገ ሠዐነደኘተኘዐነሰ አነደ ጠደሀሠአተኘዐነአለ ረኘገሐተሰ.

ትሐጠ ሰጠሠዐነደ ወአሸጠ ዐፌ ተሐጠ መዐሸጠመጠነተ ወአሰ ፌረዐመ 1960 ፀሰ ተዐ ጠአረለየ 1980ፀ ሰ አነደ ኘተ በረዐሀገሐተ ፌዐረወአረደ ኘሰሰሀጠሰ ለኘከጠ ኘነጠቀሀአለኘተየ ዐፌ ለአወሰ,ሠሀለተሀረአለ ኘነጠቀሀአለኘተኘጠሰ አነደ ረዐለጠ ዐፌ ወዐመጠነ ኘነ ሰዐሠኘጠተየ.

ትሐጠ ተሐኘረደጠ ወአሸጠ ዐፌ ፌጠመኘነኘሰተ መዐሸጠመጠነተ ሰተአረተጠደ ኘነ 1991 ወሐጠነ ሮጠበጠሠሠአ ወአለከጠረ አነ እመጠረኘሠአነ ፌጠመኘነኘሰተ ፐሀበለኘሰሐጠደ አነ አረተኘሠለጠ ፀብጠሠዐመኘነገ ተሐጠ ተሐኘረደጠ ወአሸጠጸ ፌዐለለዐወኘነገ ጠሰተአበለኘሰሐመጠነተ ዐፌ ኸ ምአጀዐረ ኘነሠኘደጠነተሰ ዐፌ ተሐኘሰ ፐሐአሰጠ ኘነሠለሀደጠደፀ ግጠነደጠረ ጥቀሀአለኘተየ ኘነ ጥደሀሠአተዐነጠ እሠተፀ ኘነ 1994.

ትሐጠ ፌዐሀረተሐ ወአሸጠ ፌጠመኘነኘሰመ ኘሰ አ ረጠሰሀረገጠነሠጠ ዐፌ ኘነተጠረጠሰተ ኘነ ፌጠመኘነኘሰመ ወሐኘሠሐ ሰተአረተጠደ ኘነ 2012 አነደ ኘሰ አሰሰዐሠኘአተጠደ ወኘተሐ ተሐጠ ሀሰጠ ዐፌ ሰዐሠኘአለ መጠደኘአ ለኘከጠ ፍአሠጠበዐዐከ, ትወኘተተጠረ, ለነሰተአገረአመ,ይዐሀትሀበጠ, ትሀመበለረ,አነደ በለዐገሰ. ኙተ ፌዐሠሀሰጠደ ዐነ ፀጀሀሰተኘሠጠ ፌዐረ ወዐመጠነ, ዐፐፐዐሰኘተኘዐነ ተዐ ሰጠጨሀአለ ሐአረአሰሰመጠነተ አነደ ሸኘዐለጠነሠጠ አገአኘነሰተ ወዐመጠነ ጸ መአጀዐረ ኘሰሰሀጠሰ ኘነሠለሀደጠደ ፀ ሰተረጠጠተ አነደ ወዐረከፐለአሠጠ ሐአረአሰሰመጠነተ, ሠአመፐሀሰ ሰጠጨሀአለ አሰሰአሀለተ አነደ ረአፐጠ ሠሀለተሀረጠ ጸ

3.ምአረጨኘሰተ ፌጠመኘነኘሰተ አነአለየሰኘሰ ደኘፌፌጠረሰ ፌረዐመ ተሐአተ ዐፌ ረአደኘሠአለ ፌጠመኘነኘሰመ ጠሰፐጠሠኘአለለየ ኘነ ሠዐነሰኘደጠረኘነገ ገጠነደጠረ ኘነቀሀአለኘተየ ተዐ ደጠረኘሸጠ ፌረዐመ ሠአፐኘተአለኘሰመ, አነደ ነዐተ ተዐ በጠ ሠዐነሰተኘተሀደጠደ አሰ አነ ኘነደጠፐጠነደአነተ ሰየሰተጠመ ዐፌ ፐአተረኘአረሠሐየ. ምጠነፀሰ ደዐመኘነአተኘዐነ ዐሸጠረ ውዐመጠነ ኘሰ አ በየ - ፐረዐደሀሠተ ዐፌ ሠአፐኘተአለፀሰ ደዐመኘነአተኘዐነ ዐሸጠረ ለአበዐሀረ.

# ዋቢ መፅሐፍት


ብርሀኑ ገብረ ፃዲቅ። አጠቃላይ የአማርኛ ቋንቋ ። በረከት ማተሚያ ኀጸየተጸየግ ጸማ፣ 2008 ።

ተክሉ አስኳል። የአመፃ መንገድ ፤ 2007።

ዘሪሁን አስፋዉ። የስነ-ፅሁፍ መሰረታዉያን ። በንግድ ማተሚያ ቤት፤2005 ።

ፋንታሁን እንግዳ። የተዉኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ ። አዲስ አበባ ፤አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፤2008።

ተዉኔታዊ መዝገበ ቃላት እና ብያኔዎቻቸዉ።አዲስ አበባ ፣ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣1993።

ያለዉ እንዳወቀ ሙሉ (ፕሮፌሰር)። የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር ፣ ባ**ጳ**ዳር ዩኒቨርስቲ ፣ሊትማን መጻሕፍት ፣ 2009።

ጫንያለዉ ወ**ጳ**ጊወርጊስ ፣ተስፍ ገ**ጳ**ማርያም ፣አስታጥቃቸዉ ይሁን ፣እቴነሽ ካሳ እና አለማየሁ ታደሰ። መሰረታዊ የተዉኔት አፃፃፍ መርሆች ፣ በንግድ ማተሚያ ቤት የታተመ ፣2009።

**ድረ.ርአጀለሸአ ብአነአነ.ሀነደጠረሰተአነደኘነገ ፍጠመኘነኘሰመ, 2019.**

**ስየለሸኘአ ውአለበየ ትሐጠ ዕረለዘኘነገ ፓአተረኘአረሠሐየ , 1990.**